PLAN INTERNATIONAL




## አቻዎች ላይ የተመሠረተ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃግብር

# የአስተዳደር ማጠቃለያ

# የአስተዳደር ማጠቃለያ

## የዚህ ሰነድ ዓላማ ምንድነው?

ፕላን ኢንተርናሽናል አቻን መሰረት ያደረገ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብር ላይ ተከታታይ ሶስት ሰነዶችን አዘጋጅቷል-

1. በአቻ ላይ የተመሠረተ የስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብር የአስተዳደር ማጠቃለያ
2. በአቻ ላይ የተመሠረተ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች    መርሃ ግብር መመሪያ
3. አቻዎች ላይ የተመሠረተ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብር -‘ጉዳትን አለማድረስ’ መመሪያ

ይህ ሰነድ ለከፍተኛ የሥራ አመራር ሠራተኞች   አቻን መሠረት ያደረገ መርሃ ግብርን በተሻለ እንዲረዱ ለማስቻል፣ በስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ውስጥ የተለያዩ በአቻ ላይ የተመሰረቱ የመርሀ ግብር አይነቶችን የማካተት ጥቅሞችን እንዲረዱ፣ የእነዚህ መርሃ ግብሮች  ጥራት ከፍ ለማድረግ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ቁልፍ ጉዳዮች እና ተጠያቂነት እንዲሁም በወጣቶች ላይ የሚደርሰውን አደጋ ወይም ጉዳት በመቀነስ ዙሪያ ባሉ ጉዳዮች ላይ የበለጥ መረዳትን ለመፍጠር የቀረበ ማጠቃለያ ነው ፤

ፕላን ኢንተርናሽናል ለብዙ ዓመታት በተለያዩ መርሃ ግብሮች እና አውዶች ውስጥ የአቻ ትምህርትን ሲጠቀም ቆይቷል።ሆኖም ፣ የአቻ ትምህርት የስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ፕሮግራም ዓላማዎችን እና የተፈለገውን ውጤት ለማሳካት;  በተፈለገው መጥን ውጤታማ ላይሆን ይችላል። በተጨማሪም ከፍተኛውን መስፈርት ግምት ውስጥ በማስገባትም በተከታታይም አይሰጥም ፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ለመፍታት በአቻዎች ላይ የተመሠረተ የስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መመሪያን አዘጋጅተናል። ይህም የፕላን ሰራተኞችን ተገቢውን አቻን መሰረት ያደረገ የስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብር   ይዘት እና አቅርቦት ጋር የተዛመዱ  “ ምንም አደጋን አለማድረስ”  የሚረዳ መመሪያ- አዘጋጅቷል

## በአቻ ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች ምንድ ናቸው? ጥቅማቸውስ?


በአቻ ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች ይለያያሉ ነገር ግን ቁልፍ ባህሪያትንም ይጋራሉ። ‘አቻወች’ ተመሳሳይ ሁኔታዎች እና ልምዶችን የሚጋሩ እና ለሌሎች ተመሳሳይ መረጃ ፣ ድጋፍ ወይም መመሪያን የሚጋሩ ሰዎችን ይገልጻል።እኛ ብዙ ጊዜ አቻዎች ተመሳሳይ ዕድሜ እንደሆኑ እናስባለን። ያሉበትን ሁኔታ እና ልምዶችን ማካፈላቸው የግል ግንኙነቶችን ለማዳበር አስፈላጊ ነው።አቻዎች ብዙውን ጊዜ በጎ ፈቃደኞች ሲሆኑ ከተለያዩ ባለሙያ አካላት ጋር  ተጨማሪ እና የተለያዩ ድጋፎችን ለማቅረብ (ለምሳሌ ፣ ከትምህርት ቤት መምህራን ወይም የጤና እንክብካቤ ሠራተኞች) ጋር አብረው ይሰራሉ። ከፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ጋርም ለመገናኘትም እንዲሁ በትብብር  ይሰራሉ ፡፡በአቻ ላይ የተመሰረቱ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ፕሮግራም  የአቻዎች ድጋፍ ፣ የአቻዎች አሰሳ ፣ የአቻዎች ምክር እና የአቻ ትምህርትን ያካትታሉ፡፡በአቻ ላይ የተመሠረተ የስነ ወሲብ እና  ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ፕሮግራም  የነዚህን እያንዳንዳቸው መርሃግብሮችን ዝርዝር በመተንተን ተገቢውን ስልት ለመምረጥ ይረዳል ፡፡[1]

በአቻዎች ላይ የተመሠረተ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች  መርሃ ግብር በወጣቶች የስነ ወሲብ እና ተዋልዶ ጤና እና መብቶች  ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ጉዳዮች ላይ ለምሳሌም; የእርግዝና መከላከያ እና ኮንዶምአጠቃቀም እና የኤችአይቪ እውቀት ላይ [2]
ውሳኔ የመወሰን በራስ መተማመናቸው ላይ  አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።የእኩያ ደጋፊ መሆን በራስ መተማመን እና በራስ-ውጤታማነት ላይ  አዎንታዊ ተፅእኖ ሊኖረው ይችላል ፣ እናም ለቀጥይ የሲቪክ ተሳትፎ ላይም ፈር ቀዳጅ በመሆን ያገለግላል ፡፡አቻዎችም የባለሙያ ሰራተኞች ለመድረስ ፈታኝ የሚሆኑባቸውን ሰዎች ተሞክሯቸውን በማጋራት እና በቀላሉ መድረስ ይችላሉ፡፡ ይህም በተለይ አቻዎች በጣም ተጽዕኖ በሚያሳድሩበት  በጉርምስና ወቅት ጊዜ በጣም ጠቃሚ ይሆናል።  አቻወች የታመኑ የመረጃ ምንጮች እና ለወጣቶችም አርአያ











[1] Another intervention is peer research, but not covered within the scope of the three resources developed.
[2] Sun et al (2016) Assessing Participation and Effectiveness of the Peer-Led Approach in Youth Sexual Health Education: Systematic Review and Meta-Analysis in More Developed Countries. The Journal of Sex Research Volume 55, 2018 - Issue 1

# በአቻዎች ላይ የተመሠረተ መርሃ ግብር ቁልፍ ጉዳዮች ምንድናቸው?

በአቻዎች ላይ የተመሠረተ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ መርሃ ግብር በጣም ውጤታማ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ጥራታቸውን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ኢንቬስትሜንት እና ድጋፍ ይፈልጋል። እናም እንደ ‹ዝቅተኛ ውጤት› መፍትሔ ወይም በቀላሉ ‹የወጣቶችን ተሳትፎ› ለማሳየት ሲባል ተግባራዊ መሆን የለባቸውም።የአቻ-ተኮር መርሃ ግብሮችን አግባብነት ያላችውን ይዘቶችችን ግምት ውሰጥ ማስገባት እና ፣ አቅርቦታቸውን ለመደገፍ የሚረዱ መንገዶችን እና ለትግበራ የሚመች አከባቢን ክግምት ወስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው




## ይዘት



አቻዎች የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ትክክለኛ ፣ ተዛማጅ እና ለአውዱ ተስማሚ መሆን አለባቸው ፡፡አቻዎች የሠለጡኑ ባለሙያዎች አይደሉም እናም በእነሱ ላይ የተቀመጡት ተስፋዎች ተጨባጭ መሆን አለባቸው ፡፡ለምሳሌ ፣ የአቻዎች አስተማሪዎች ይህ የአቻ መማሪያ ስላልሆነ የአስተማሪን ቦታ መውሰድ እና በክፍል ፊት ለፊት ተማሪዎችን ማስተማር ተገቢ አይደለም ፡፡በትምህርት ቤቶች ሁሉን አካታች የሆነ የስነ ወሲብ ትምህርትን ለማሠልጠን የሰለጠኑ እና በራስ የሚተማመኑ መምህራን ከሌሉ ፕላን ኢንተርናሽናል ይህንን ክፍተት ለመቅረፍ በመምህራን ሥልጠና ላይ ኢንቬስት ማድረግ አለበት ፡፡አቻዎች ዝርዝር ሙያዊ ይዘቶችን እንዲያቀርቡ አይጠበቅም - ለምሳሌ- ለማሰልጥን ዝግጁነት በሌላቸው ርዐሶች ላይ ለምሳሌ; በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታ ምልክቶች ወይም በወሲባዊ ጥቃት እና / ወይም ብዝበዛ ላይ ውይይቶች እንዲያደርጉ አይጠበቁም። በማህበረሰብ ላይ ያልተጠበቀ ተቃዉሞን በሚያስከትሉ ወይም ለአደጋ እና ለጉዳት ሊያጋልጣቸው የሚችሉ ስሜታዊ ርዕሶች ላይ ውይይት እንዲመሩ መጠበቅ አግባብ አይደለም።ለአቻዎች ትርጉም ያላቸው ተግባራት ወጣቶችን በወሲብ እና እና በግንኙነቶች ዙሪያ ስላለው አመለካከት እና እሴቶች እንዲያስቡ የሚያበረታቱ አሳታፊ እንቅስቃሴዎችን እና ውይይቶችን ማከናወን፣ አደጋን መመርመር እና መገምገም; በራስ መተማመንን ፣ ድርድርን እና ውሳኔ አሰጣጥን የሚደግፉ ክህሎቶችን በማዳበር ረገድ ቢሰሩ ነው ፡፡ አቻወች በወጣት መብቶች እና በስምምነት ዙሪያ ያሉ ጉዳዮች ላይ መስራታቸው ተገቢ ነው ፡፡ በተጨማሪም ወጣቶችን ወደ ተጨማሪ ድጋፍ እና አገልግሎቶች መምራት እና ማመልከት መቻል አለባቸው ፡፡ይዘቶቹ እና መልእክቶቹ በፕላን ኢንተርናሽናል በስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ እሴቶች እና መርሆች እና በተሟላ የስነ ወሲብ ትምህርት ላይ ያሉ የጥራት ደረጃዎች ጋር መጣጣም አለባቸው ፡፡እነዚህን መመዘኛዎች የሚቃረኑ ብሔራዊ ሥርዓተ-ትምህርት የአቻዎች መርሃ ግብሮችን - ለምሳሌ በመታቀብ ላይ የተመሰረቱ መልዕክቶች ወይም ግብረ ሰዶማዊነትን አስመልክቶ አድሎአዊ መልዕክቶችን ማስተዋወቅን ጨምሮ - መጠቀም አይቻልም ፡፡

## አሰጣጥ



በአቻዎች ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች ውጤታማ እንዲሆኑ ከፍተኛ ኢንቬስትሜንት ፣ ድጋፍ እና ተጨማሪ ይዘቶች ያስፈልጋሉ ፡፡አቻዎች ከባለሙያዎች የመጀመሪያ እና የክትትል ስልጠና እንዲሁም ቀጣይነት ያለው ቁጥጥር እና ምክር ይፈልጋሉ። ይህም ስጋቶችን ለመጋራት ፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለመወያየት እና ልምዶቻቸውን ለማሻሻል ይረዳል።በትክክል ያልተደገፉ አቻዎች እነሱ ለማቅረብ ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ባልሆኑባቸው ወይም መረጃ በሌላቸው ጉዳዮች ላይ ምክር ሊሰጡ ይችላሉ። እናም መልሶቹን በማያውቋቸው ነገሮች ላይ መልስ እንዲሰጡ ግፊት ሊሰማቸው ይችላል ፡ ፡ ይህ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ እንዲሰራጭ እና በአቻዎች ላይ ያለውን እምነት ሊያሳጣ ይችላል ፡፡ አቻዎችም ፍላሽ ካርዶችን ፣ ስዕሎችን፣ ጥያቄዎችን ፣ ቀላል የክፍለ-ጊዜ ዝርዝር እና የፈጠራ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ ሥራቸውን ለመደገፍ ግልፅ እና ቀላል ሀብቶችን መጥቀም ያስፈልጋቸዋል፡፡በአቻዎች ላይ የተመሠረተ መርሃ ግብር አበሎችን / ድጎማዎችን እንዲሁም አቻወች በሥራቸው ላይ የሚያጋጥማቸውን ማንኛውንም ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን የሚያስችል በቂ የገንዘብ ምንጭ ያስፈልጋቸዋል። ስብሰባዎችን ወይም ስልጠናዎችን ለመከታተል የራሳቸውን ገንዘብ እንዲጠቀሙ አይጠበቅባቸውም ፡፡በአንዳንድ ሁኔታዎች ለሥራ የሚከፈል ክፍያ በጣም ተገቢ ካሳ ይሆናል ፡፡[3]

## ድባብ



አፈጻጸሙን የተሳካ እንዲሆን የሚረዱ ድጋፍ ሰጪ አከባቢ መኖሩን ለማረጋገጥ አቻዎች ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች የሰፊ መርሃ ግብር አካል ሆነው መተግበር አለባቸው ፡ ፡በአቻዎች ላይ የተመሠረተ መርሃ ግብር በተናጥል ሲሰጥ ውስን ተጽዕኖ ብቻ ይኖረዋል፡ ፡ይልቁንም ፣ ከሰፊ እና ተደጋጋፊ እንዲሁም ጠንካራ ትስስርን ከሚያካትቱ መርሃ ግብሮች ጋር ለምሳሌም ለወጣቶች ተስማሚ ከሆኑ እና የሰርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጭ አገልግሎቶች መርሃ ግብሮች ጋር መካተት አለባቸው ፡፡ አቻዎች በጤና ፣ በትምህርት ወይም በማኅበራዊ እንክብካቤ ሥርዓት ውስጥ መሥራት ይኖርባቸዋል። ፕላን ኢንተርናሽናልም አስፈላጊውን ሙያዊ እና የጉዳይ አስተዳደር ድጋፍን ማግኘታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። እንዲሁም ፕላን ኢንተርናሽናል ከማኅበረሰቦች ጋር ትብብርን እና መተማመንን መፍጠር እና ያልተጠበቁ ተቃዉሞዎች እና ጉዳቶች እንዳይደርሱ ድጋፍ መኖሩን ማረጋገጥ አለበት ፡፡አቻዎች ተግባራቸውን ያለ ትንኮሳ እና አደጋን ለማከናወን አስተማማኝ ቦታ ይፈልጋሉ ፡፡ መርሃግብሮች ደህንነታቸውን የሚያረጋግጡ ተጨማሪ የደህንነት ዘዴዎችን መዘርጋት አለባቸው ፣ ለምሳሌ ፣ በሚመጥን ቦታ ጥንድ ሆነው እንዲሰሩ የማድረግ እና አቻዎች ከስራ ሲመለሱ ‘ተመዝግቦ የመግባት’ ስርዓት መዘርጋት አለባቸው።የአቻዎች እና የፕሮግራም ተሳታፊዎችን ደህንነት ማረጋገጥ ወሳኝ ነው። በፕላን ኢንተርናሽናል የድህንነት ጥበቃ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ጥሰቶችን ሪፖርት ስለማድረግ እና ምላሽ ስለመስጠት ያሉ መመሪያዎችን ለመረዳት እና ተግባራዊ ለማድረግ አቻዎች ተገቢ ሥልጠና እና ድጋፍ ይፈልጋሉ ፡፡አቻዎች ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች እንደ ሰፊ የድርጊቶች ጥቅል አካል ሲሰጡ ለስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ፕሮግራሞች ላይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሊያበረክቱ ይችላሉ። ነገር ግን በተከታታይ ወደ በከፍተኛ ጥራት እንዲሰጡ ተገቢውን ኢንቬስትመንት ፣ ሥልጠና ፣ ድጋፍ እና ቁጥጥር ይፈልጋሉ ፡፡

[3] Plan International (2021) A Recommended Framework for Volunteerism and Compensation for Young People.

ይህ ጽሑፍ በፊንላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር (ኤምኤፍኤ) የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ነው። ኤምኤፍኤ ፊንላንድ በዚህ የተገለጹትን አስተያየቶች አይጋራም። የይዘቱ ብቸኛ ኃላፊነት የፕላን ኢንተርናሽናል ነው

With support from Finland's development cooperation

በመጀመሪያ በ 2013 ታተመ

Text © ፕላን ኢንተርናሽናል 2013. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው
ቅድመ ፈቃድ ሳይኖር የዚህ ጽሑፍ ክፍል በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ በኤሌክትሮኒክ ፣ በሜካኒካል በፎቶ ኮፒ ወይም በሌላ መንገድ ሊባዛ ወይም ሊተላለፍ አይችልም።

ፕላን ኢንተርናሽናል (2021). የስነ ወሲብ እና ሥነ-ተዋልዶ ጤና እና መብቶች አቻ-ተኮር መርሃ ግብር ፡ የአስተዳደር ማጠቃለያ ዩናይትድ ኪንግደም፡ ፕላን ኢንተርናሽናል

ትርጉም በማህደር ተስፉ የሻው